# የሐዋርያው ዮሐንስ መልእክት – ሦስተኛ

1ሽማግሌው፤

በእውነት ለምወደው ለውድ ወዳጄ፣ ለጋ
ይዮስ፤

2ወዳጅ ሆይ፤ ነፍስህ በመልካም ሁኔታ
ላይ እንዳለች ሁሉ መልካም ጤንነት እን
ዲኖርህና በነገር ሁሉ እንዲሳካልህ እጸል
ያለሁ። 3ለእውነት ታማኝ እንደሆንህና የም
ትመላለሰውም በእውነት እንደ ሆነ አንዳ
ንድ ወንድሞች መጥተው ስለ አንተ ሲመ
ሰክሩልኝ እጅግ ደስ አለኝ። 4ልጆቼ በእ
ውነት የሚመላለሱ መሆናቸውን ከመስ
ማት የሚበልጥ ደስታ የለኝም።

5ወዳጅ ሆይ፤ ለአንተ እንግዶች ቢሆ
ኑም እንኳ ለወንድሞች በምታደርገው
ነገር ሁሉ ታማኝ ነህ። 6እነርሱ አንተ
ስላለህ ፍቅር በቤተ ክርስቲያን ፊት መስክረ
ዋል፤ በመንገዳቸውም እግዚአብሔርን ደስ በሚ
ያሰኝ ሁኔታ ብትረዳቸው መልካም ታደር
ጋለህ፤ 7ስለ ስሙ የወጡት ከአሕዛብ ምንም
ሳይቀበሉ ነውና። 8እንግዲህ አብረን ለእው
ነት እንድንሠራ እንዲህ ያሉትን ሰዎች
ልናስተናግድ ይገባናል።

9ለቤተ ክርስቲያኒቱ ጽፌ ነበር፤ ነገር
ግን መሪ መሆን የሚወደው ዲዮጥራጢስ
አይቀበለንም። 10ስለዚህ እኔ ከመጣሁ
እርሱ በክፉ ቃላት ስማችንን ለማጥፋት
የሚያደርገውን ሁሉ ይፋ አወጣለሁ፤ ይህም
አልበቃ ብሎት ወንድሞችን አይቀበልም፤
ሊቀበሏቸው የሚፈልጉትን ይከለክላቸዋል፤
ከቤተ ክርስቲያንም ያስወጣቸዋል።

11ወዳጅ ሆይ፤ መልካም የሆነውን እንጂ
ክፉውን አትምሰል። መልካም የሆነውን
የሚያደርግ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው። ክፉ
የሚያደርግ ግን እግዚአብሔርን አላየውም።
12ለድሜጥሮስ፣ ሰው ሁሉ ይመሰክርለታል፤
እውነት ራሷም ትመሰክርለታለች፤ እኛ ደግሞ
እንመሰክርለታለን፤ እናንተም ምስክርነታ
ችን እውነት እንደ ሆነ ታውቃላችሁ። 13የም
ጽፍልህ ብዙ ነገር ነበረኝ፤ ይሁን እንጂ
በቀለምና በብርዕ እንዲሆን አልፈልግም፤
14በቅርቡ ላይህ ተስፋ አደርጋለሁ፤ ፊት
ለፊትም እንነጋገራለን። 15ሰላም ለአንተ
ይሁን፤ ወዳጆች ሰላምታ ያቀርቡልሃል።
ለወዳጆች በየስማቸው ሰላምታ አቅርብልኝ።

1፥1 ሐሥ11፥30፤ 2ዮሐ1
1፥3 ቆኦ5፡10፤ ሐሥ1፥16፤2ዮሐ4
1፥4 ቆኦ3፤1ዮሐ2፥1
1፥5 ቆኦ3፤ ሮሜ12፥13፤ዕብ13፥2
1፥6 1ቆሮ16፥11፤ 2ቆሮ1፥16፤ኤፌ4፥1
1፥7 ዮሐ15፥21፤ ሐሥ20፥33፡35
1፥10 ቆኦ5፡14፤ ዮሐ9፥22፡34፤ 2ዮሐ12
1፥11 መዝ34፥14፤ 37፥27፤1ዮሐ2፥29፤ 3፥6፡9፡10
1፥12 ዮሐ19፥35፤ 21፥24፤1ጢሞ3፥7
1፥14 ዮሐ10፥3፤ ሮሜ1፥7፤ኤፌ6፥23፤ 2ዮሐ12